# የአዞ እምባ

ከጌትነት ኖርዌ

ምነው እስከዛሬ እርማችንን በልተን
አሉ ውይስ የሉም እያልን ስንማስን
ቡከኑ ወያኔ እኛን ማርዳት ፈርቶ
በዝጉ ወህኒ ቤት ሥጋ መትሮ በልቶ
አጥንትንም ወቅጦ ደምንም ጠጥቶ
በጥበት አዶከበሬው አጓርቶ
ንፁህን ታጋዮችን አሰቃይቶ
በጉርጓድ እስር ቤት አፍኖ
በሀሰት ወንጀሎና ኮንኖ
መርዶ አርጅ ላከብን
የአዞ እምባ አምቢዎችን
እናም እነ አያ እንቶኔ ብቅ አሉ
በአዞ እምባቸው ሊያስመስሉ
በማይመለከታቸው ሊቀባጥሩ
መለስ ብለው ሊያጋፍሩ
የአዛኝ ቅቤ አንጓች ተላላኪ
ጽናተ ቢስ ሆድ አምላኪ
እየተገዛችሁ ታገሉ ባይ
ትግል አምካኝ አድርባይ
ዞረው ይምጡ ሊያረዱን
ሲኮንኑ እንዳልሰማን
እንደነርሱማ ብንሆን
አጎንብሰን በተደፋን
ጆሮ ዳባ ልበስ ብለን በተኛን
የምዝብሩ ሲቃ ባልተሰማን
በንጹሃን የደም አባላ በጨቀየን
ግና ታጋይ ቢሞት ታጋይ ይተካል
ትግሉ አይሞትም ይቀጥላል
ሺዎችን በሚሊዮኖች ተክቶ
ይጥላል የገማን ሥርአት አንኮታክቶ